የኢትዮጵያ ሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት
Ethiopian Meteorology Institute

# ወርሃዊ የአየር ጠባይ
# ግምገማና እና ትንበያ መጽሔት

## ከጁላይ 1-31/2023 የነበረው የአየር
## ጠባይ ግምገማ እንዲሁም

## ከኦገስት 1-31/2023 የሚኖረው የአየር
## ጠባይ ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

ኦገስት 2023
አዲስ አበባ

**ርዕስ** **ገፅ**

እ.ኤ.አ ከጁላይ 1 እስከ 31/2023 የነበረው የአየር ጠባይ ግምገማ....1
ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከጁላይ 1 እስከ 31/2023 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ....3
ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከጁላይ 1 እስከ 31/2023 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት....4
ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከጁላይ 1 እስከ 31/2023 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ከመደበኛው....4
ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር....4
እ.ኤ.አ ከጁላይ 1 እስከ 31/2023 የነበረው የአየር ጠባይ በእርሻ....5
ሥራ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ....5
ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከጁላይ 1 እስከ 31/2023 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ....5
እ.ኤ.አ ከጁላይ 1 እስከ 31/2023 የነበረው የአየር ጠባይ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ....6
ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከጁላይ 1 እስከ 31/2023 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ....6
እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 31/2023 የሚኖረው የአየር....7
ጠባይ አዝማሚያ....7
ካርታ 6 ከኦገስት 1 እስከ 31/2023 ድረስ የሚኖረው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር....8


## እ.ኤ.አ ከጁላይ 1 እስከ 31/2023 የነበረው የአየር ጠባይ ግምገማ

በመደበኛ ሁኔታ በጁላይ ወር የክረምት ዝናብ ሰጪ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በሀገሪቱ የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ የሆኑ ስፍራዎች ላይ እየተስፋፉ እና እየተጠናከረ በመሄድ ዝናቡ ከክረምት ዝናብ ሰጪ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች መጠናከር ጋር ተያይዞ በምዕራብ፣ደቡብ፣ደቡብ ምዕራብ እና መካከለኛ ው እንዲሁም ሰሜን ምስራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተስፋፋ ነበር፡፡

ባለፈው ጁላይ ወር የመጀመሪያው አስር ቀናት የዝናቡ ስርጭት በምዕራብ፣በደቡብ ምዕራብ እና መካከለኛዉ እንዲሁም ደቡብ ብሔር ብሄረሰቦች እና ህዝቦች ክልል የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ የተሻለ የዝናብ ስርጭት ነበራቸው፡፡ በሁለተኛው አስር ቀናትም በምዕራብ የሀገሪቱ ዳርቻዎች ላይ እንዲሁም አልፎ አልፎ በምስራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ እየተስፋፋ ነበር፡፡ ነገር ግን በሶስተኛው አስር ቀናት የዝናቡ ስርጭት ከቦታ ሽፋን አንጻር ሲገመገም በሀገሪቱ የክረምት ተጠቃሚ የሆኑ አከባቢዎችን ያላዳረሰ ነበር፡፡ በጁላይ ወር ዉስጥ ከባድ ዝናብ ከተመዘገበባቸው ስፍራዎች መካከል በአዲስ አበባ ቦሌ 33.0፣37.8፣በአዲስ አበባ ኦብዘርቫቶሪ 34.4፣ በአዴት 30.0፣ በአይራ 40.2፣32.2፣ በሀሮማያ 32.6፣ በአልጌ 30.0፣45.0፣34.0፣45.0፣70.0፣በአማን 40.0፣31.4፣ በአምባ ማሪያም 34.6፣37.6፣ አምደወርቅ 65.5፣ በአርጆ 30.4፣ በአርሲ ሮቤ 33.2፣ በአሶሳ 34.8፣ በአዋሽ አርባ 79.0፣ በአይከል 45.9፣ በባህርዳር 30.5፣78.2፣42.7፣34.5፣46.1፣33.9፣ በባቲ 30.0፣ በበደሌ 45.3፣38.2፣36.2፣ በቦሬ 46.0፣ በቡኢ 32.5፣ በቻግኒ 35.0፣32.2፣ በጭፍራ 50.6፣ በደብረ ብርሃን 46.0፣ በደብረታቦር 38.0፣32.0፣ በዳሊፋጊ 46.3፣ በዳንግላ 31.0፣60.5፣40.7፣ በደባርቅ 34.6፣47.0፣ በደብረ ማርቆስ 34.2፣32.3፣30.5፣32.8፣30.5፣ በደብረ ወርቅ 32.6፣72.0፣44.6፣በቢሾፍቱ 36.8፣42.6፣በኢጃጂ 30.2፣59.2፣በፍቼ 48.2፣36.1፣34.7፣ በፉኚዶ 38.8፣ በጋምቤላ 35.3፣ በጋቲራ 30.2፣39.5፣ በገዋኔ 33.0፣ በጊዳአያና 42.5፣76.0፣68.4፣ በጊምቢ 35.1፣62.5፣70.3፣ በጎንደር 47.5፣47.0፣ በጎሬ 53.7፣38.0፣43.0፣በጉንዶ መስቀል 57.7፣48.6፣36.0፣ በሀረር 30.5፣ በጃራ 31.6፣ በካቺሴ 37.7፣37.8፣35.0፣38.2፣36.4፣30.8፣ በሊሙገነት 33.4፣37.5፣59.0፣ በማጂ 30.0፣ በማሻ 40.6፣30.6፣ በሜኤሶ 30.9፣ በመተሃራ 47.7፣41.0፣41.8፣ በመተማ 34.5፣32.2፣ በሞጣ 30.0፣ በአዳማ 46.4፣31.6፣32.9፣50.2፣ በነጆ 43.4፣52.6፣ በነቀምቴ 34.4፣51.5፣32.9፣65.8፣32.7፣ በኑራኤራ 32.2፣41.0፣ በፓዊ 30.4፣32.2፣38.5፣ በሰኮሩ 34.5፣ በሻዉራ 37.6፣36.4፣36.7፣30.4፣በሻምቡ 40.0፣37.4፣ በሽርቆሌ 37.2፣ በሾላገበያ 38.0፣34.2፣36.0፣ በቴፒ 43.6፣ በወገልጤና 38.7፣ በወላይታ ሶዶ 30.7፣ በየትኖራ 46.9 እንዲሁም በባቱ 35.0፣30.3 በሚ.ሜ ይገኙበታል፡፡ በሌላ በኩል የቀኑ

ከፍተኛ የሙቀት መጠን በምዕራብ እና በደቡብ ምዕራብ፣ በሰሜን ምስራቅ፣ በደቡብ ምሥራቅ እና በደቡብ የሀገሪቱ ዳርቻዎች ላይ በአብዛኛዎቹ ቀናት ላይ ከ40 ዲ.ሴ በላይ ሆኖ ተመዝግቧል (ምስል 1)።

ከ40 ዲ.ሴ በላይ የተመዘገበባቸውን ሥፍራዎች ለመጥቀስም ያህል





ምስል 1 የቀኑ ከፍተኛ የሙቀት መጠን በዲ.ሴ


ባለፈው የጁላይ ወር የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ ቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም፤ከኦሮሚያ ክልል ምስራቅ እና ምዕራብ ወለጋ፣ሆሮ ጉዱሩ፣ ቄለም ወለጋ፣ ኢሉ አባቦራ፣ምስራቅ እና ምዕራብ ሸዋ፣አርሲ እና ምዕራብ አርሲ፣ምስራቅ እና ምዕራብ ሀረርጌ፤ከአማራ ክልል ሰሜን፣ምዕራብ እና ማዕከላዊ ጎንደር፣ምስራቅ እና ምዕራብ ጎጃም፣አዊ ዞን፣ዋግምራ፣ሰሜን እና ደቡብ ወሎ፤ከጋምቤላ ክልል ኢታንግ ልዩ ወረዳ፣ኑዌር፣አኙዋክ እና ማጃንግ ዞን፣ከቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል አሶሳ፣ካማሺ፣መተከል ዞን፣ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ምዕራብ ኦሞ፣ባስኬቶ፣ ከደቡብ ብሄር ብሄረሰቦች እና ህዝቦች ክልል ከምባታ ጠንባሮ፣ዳዉሮ፣ወላይታ ሶዶ፣ሀዲያ፣ጉራጌ፣ስልጤ፣ሀላባ እና ጌዲኦ፣ከሱማሌ ክልል ሲቲ ዞን፤ከአፋር ክልል ዞን 1 እና 4፤ በአዲስ አበባ፣ በድሬዳዋና ሐረሪ ላይ ከ51-565 ሚ.ሜ የሚደርስ ከ1-30 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 1 እና 2) ።

ባለፈው የጁላይ ወር የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር ከአማራ ክልል በማዕከላዊ ፣ምዕራብ እና ደቡብ ጎንደር፣አዊ ዞን፣ምስራቅ እና ምዕራብ ጎጃም፣በሰሜን እና ደቡብ ወሎ፣ሰሜን


ሸዋ፣ከኦሮሚያ ክልል ምስራቅ እና ምዕራብ ወለጋ፣ቄለም ወለጋ፣ቡኖ በደሌ፣ኢሉ አባቦራ፣ሆሮ ጉዱሩ ወለጋ፣ምስራቅ እና ምዕራብ ቤኒሻንጉልጉሙዝ ክልል አሶሳ፣ካማሺ፣ በአዲስ አበባ እና በድሬዳዋ ላይ መደበኛና ከመደበኛ በላይ ዝናብ የተመዘገበ ሲሆን፤ የተቀሩት የጋምቤላ፣ የትግራይ፣ የቤንሻንጉል ጉምዝ፣የሱማሌ እና የአፋር ክልል ዞኖች ላይ ከመደበኛው በታች የሆነ የዝናብ መጠን ተመዝግቧል (ካርታ 3) ፡፡




ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከጁላይ 1 እስከ 31/2023 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ




ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከጁላይ 1 እስከ 31/2023 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት





ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከጁላይ 1 እስከ 31/2023 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር

## ኢ.ኤ.አ ከጁላይ 1 እስከ 31/2023 የነበረው የአየር ጠባይ በእርሻ ሥራ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

በመደበኛ ሁኔታ የጁላይ ወር ለክረምት ዝናብ መኖር አመቺ ሁኔታ የሚፈጥሩ የአየር ሁኔታ ክስተቶች ከመኖራቸዉ ጋር ተያይዞ አስቀድመው የተዘሩ ሰብሎች ለእድገት የሚያስፈልጋቸወን በመጠን ከፍ ያለ እርጥበት የሚያገኙበት ጊዜ ነው፡፡


ባሳለፍነዉ የጁላይ ወር የመጀመሪያው አስር ቀናት በምዕራብ፣ በደቡብ ምዕራብ እና መካከለኛዉ እንዲሁም ደቡብ ብሔር ብሄረሰቦች እና ህዝቦች ክልል እንዲሁም በሁለተኛው አስር ቀናትም በምዕራብ የሀገሪቱ ዳርቻዎችና አልፎ አልፎ በምስራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ የተስፋፋ የእርጥበት ስርጭት የነበር ሲሆን በአንጻሩ ግን በሶስተኛው አስር ቀናት የእርጥበት ስርጭቱ የተወሰኑ የክረምት ተጠቃሚ አከባቢዎችን ያላዳረሰ ነበር፡፡ በአጠቃላይ ባሳለፈነው የጁላይ ወር ለክረምት ዝናብ መፈጠር መንስኤ የሆኑ የአየር ሁኔታ ክስተቶች በመዳከማቸዉ ከመካከለኛው፣ ከምዕራብ እና ደቡብ ምዕራብ ጥቂት ቦታዎች በስተቀር አብዛኛዉ የክረምት ተጠቃሚ አከባቢዎች ላይ አነስተኛ የእርጥበት መጠንና ስርጭት ነበራቸዉ፡፡ ይህም ሁኔታ ከጁላይ ጀምሮ ለሚዘሩ የተለያዩ የመካከለኛ ጊዜ ሰብሎች ለመዝራትና በታቀደዉ መሰረት የግብርና እንቅስቃሴን ለማከናወን አሉታዊ ጎን ቢኖረውም፤ አስቀድምው ተዘርተው በተለያየ የእድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ የመኽር ሰብሎች የውኃ ፍላጎታቸውን ከሟሟላት አንፃር የጎላ ሚና ከመኖሩም በላይ ከኤፕሪል ጀምሮ ቀደም ብለው ለተዘሩ እንደ በቆሎና ማሽላ ለመሳሰሉ የረጅም ጊዜ የመኽር ሰብሎች እንዲሁም ለተለያዩ ቋሚ ተክሎች በተሟላ ሁኔታ እንዲያድጉ የጎላ አስተዋፅዖ ነበረው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በአርብቶ አደርና በከፊል የአርብቶ አደር አካባቢዎች የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ለግጦሽ ሳርና ለመጠጥ ውኃ አቅርቦት አዎንታዊ አስተዋፅዖ ነበረው፡፡ በሌላ በኩል በአንዳንድ አካባቢዎች ላይ የነበረው ከባድ የዝናብ መጠን በመደበኛ ባህሪያቸው በእርጥበት መብዛት በሚታወቁ ሰፍራዎች ላይ ለጎርፍ መከሰትና የመሬት መንሸራተት እንዲሁም በአንዳንድ ስፍራዎች ላይ በሰብል ማሳዎች ላይ የውሃ መተኛትን ያስከተለ ሲሆን ይህም ሁኔታ እየተከናወነ በሚገኘው የእርሻ ስራ እንቅስቃሴ ላይ አሉታዊ ጎን ነበረው (ካርታ 4)፡፡




ካርታ 4 ኢ.ኤ.አ ከጁላይ 1 እስከ 31/2023 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ

## እ.ኤ.አ ከጁላይ 1 እስከ 31/2023 የነበረው የአየር ጠባይ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባለፈው የጁላይ ወር የነበረው የአየር ጠባይ በውኃው ዘርፍ ላይ የነበረው ተፅዕኖ በደቡብ ምዕራብ፣ በምዕራብ እና በሰሜን ምዕራብ የሀገሪቱ ተፋሰሶች ላይ ተጠናክሮ ተስተውሎ ነበር ። ከነዚህም በአብዛኛው አባይ፣ ኦሞ ጊቤ የላይኛውና የመካከለኛው ባሮ አኮቦ፣ አዋሽ፣ በላይኛው ገናሌ ዳዋና ስምጥ ሸለቆ እንዲሁም በጥቂት የላይኛው ዋቤ ሸበሌ ተፋሰሶች ላይ ከከፍተኛ እስከ በጣም ከፍተኛ የደረሰ እርጥበት መጠን እንደነበራቸው የተገመገሙ የውሃ ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመለክታሉ።በተጨማሪም በመካከለኛው አዋሽ፣ ዋቤ ሸበሌ፣ ስምጥ ሸለቆ እንዲሁም በታችኛው ኦሞ ጊቤ ፋሰሶች ላይ መጠነኛ እርጥበት ነበራቸው።ከዚህም ጋር ተያይዞ የክረምት እርጥበት ተጠቃሚ በሆኑት የሀገሪቱ ተፋሰሶች ላይ በሚገኙ ዋና ዋና ተፋሰሶች የነበረው የተሻለ የእርጥበት ለውሃ ሀብት መጠን መጨመር ረገድ አዎንተዊ አስተዋፅዖ ነበረው (ካርታ 5) ፡፡





ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከጁላይ 1 እስከ 31/2023 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ

# እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 31/2023 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ

በመደበኛ ሁኔታ የኦገስት ወር ካልፉት የክረምት ወራት በተሻለ ሁኔታ ሁሉንም የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎችን በመጠንም ሆነ በሥርጭት ከፍተኛ መጠን የሚደርስበት ወር ነው። ከዚህም ጋር ተያይዞ በአንዳንድ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ለተከታታይ ሰዓትና ቀናት የሚዘንብበትና በተጨማሪም በፀሐይ ሀይል ታግዘዉ ከሚፈጠሩ የደመና ክምችቶች በረዶ የቀላቀለ ከባድ ዝናብ አልፎ አልፎ የሚስተዋልበት ሲሆን ከዚሁ ጋር ተያይዞ ለወንዞች ሙላትና ቅጽበታዊ ጎርፍ የሚከሰትበት ጊዜ ነዉ።

በመደበኛ ሁኔታ የኦገስት ወር የክረምት ዝናብ በመጠንም ሆነ በሥርጭት በክረምት ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎች ላይ ከፍተኛ ደረጃ የሚደርስበት ጊዜ ነው። በተጨማሪም በኦገስት ወር በአንዳንድ ቦታዎች ላይ በፀሐይ ሀይል ታግዘዉ ከሚፈጠሩ የደመና ክምችቶች በረዶ የቀላቀለ ቅጽበታዊ ጎርፍ ሊያስከትል የሚችል ከባድ ዝናብ አልፎ አልፎ ሊኖር እንደሚችል የትንበያ መረጃዎች ያሳያሉ። በመጪው የኦገስት ወር ዝናብ ሰጪ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ካለፈዉ ወር አኳያ በሰሜን ምስራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በአንፃራዊነት የመዳከም አዝማሚያ ሊኖር እንደሚችል የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ። ይሁን እንጂ አልፎ አልፎ ከሚጠናከሩት ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ጋር ተያይዞ በተለይም በሰሜን ምስራቅ፣ በሰሜን፣ በመካከለኛዉ፣ በደቡብ ምዕራብና በምዕራብ የሃገሪቱ ቦታዎች ላይ ከሚጠናከሩ የደመና ክምችቶች የተነሳ ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ እንደሚኖራቸው የአሃዛዊ ትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ።

በአጠቃላይ በሚቀጥለው ወር ከኦሮሚያ ክልል የምዕራብ ወለጋ ፣ ሆሩ ጉዱሩ ፣ ቄለም ወለጋ፤ ኢሉአባቦራ፤ሁሉም የሸዋ ዞኖች፣ ጅማ፣ ቡኖ በደሌ፤ አዲስ አበባ፤ በጥቂት የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ዞኖች፤ ከደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክልል የጉራጌና የስልጤ ዞኖች፤ አብዛኞዎቹ የአማራ ክልል እና የትግራይ ክልል ዞኖች ከመደበኛው ጋር የተቀራረበ እና ከመደበኛ በላይ ዝናብ ያገኛሉ። ከዚህም ሌላ ከደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል ደግሞ የሀድያ ዞኖች፣ የወላይታ፣ ጌዲዮ፤ የአፋር ክልል ዞኖች እንዲሁም የሲዳማ እና የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ዞኖች፤ ከኦሮሚያ ክልል የምስራቅ ወለጋ፣ አርሲ እና የምዕራብ አርሲ ዞኖች፣ ምስራቅና ምዕራብ ሐረርጌ፤ ድሬዳዋና ሐረሪ፤ ሁሉም የጋምቤላ ዞኖች፤ ከሶማሌ ክልል ሲቲ እና የፋፈን ዞኖች ከሚኖራቸው እርጥበት አዘል አየር ጋር ተያይዞ በአብዛኛው ከመደበኛው ጋር የተቀራረበ እና በአንዳንድ ቦታዎች ላይ ከመደበኛ በታች የዝናብ መጠን እንደሚኖራቸው ይጠበቃል።




ካርታ 6 ከኦገስት 1 እስከ 31/2023 ድረስ የሚኖረው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር

## እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 31/2023 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

የኦገስት ወር በመደበኛ ሁኔታ ከሌሎቹ የክረምት ወራት ሲታይ የእርጥበት ሁኔታው በአብዛኛው የመኸር አብቃይ አካባቢዎች ላይ ከእርጥበታማ (Moist) እስከ በጣም እርጥበታማ (Hyper Humid) ሁኔታ የሚያመዘንበት ወር ነው፡፡

በመጪው የኦገስት ወር ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በሰሜን ምስራቅ የሀገሪቱ ሥፍራዎች ካለፈዉ ወር አኳያ በአንፃራዊነት የመዳከም አዝማሚያ ሊኖር እንደሚችል እና ከዚሁም ጋር ተያይዞ በነዚህ ሥፍራዎች የሚገኘው የእርጥበት በመጠንም የመቀነስ አዝማሚያ ይኖረዋል፡፡ ይህም ሁኔታ የመኸር ወቅት እርሻ እንቅስቃሴን በመደበኛ ሁኔታ ዘግይተው ለጀምሩና በሰሜን ምስራቅ ለሚገኙ አርብቶ አደር አካባቢዎች ላይ ለሚጠበቀው የግብርና እንቅስቃሴ አሉታዊ ጎን የሚኖረው ቢሆንም በተለይም ባሳለፍናቸው ቀናት አካባቢዎቹ ሲያገኙት ከነበረው እርጥበት አንፃር የከፋ ጉዳት ባያስከትልም የሚገኘውን አነስተኛ እርጥበት በተገቢው መንገድ መጠቀም እንዳለባቸው ይመከራል፡፡ ይሁን እንጂ በተለይም በሰሜን ምስራቅ፣ በሰሜን፣ በመካከለኛዉ፣ በደቡብ ምዕራብና በምዕራብ የሃገሪቱ ቦታዎች ላይ ከሚጠናከሩ የደመና ክምችቶች የተነሳ ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለዉ እርጥበት ሊኖር እንደሚችል የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ። ይህም ሁኔታ የአፈር ውስጥ እርጥበትን ከማሻሻል አንፃር አስቀድመው የተዘሩና በተለያየ የዕድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ የመኸር ሰብሎች እንዲሁም ለተለያዩ የቋሚ ተክሎችና የጓሮ አትክልቶች የውሃ ፍላጎታቸውን ከማሟላት አንፃር ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡ በተጨማሪም በምስራቅና በሰሜን ምስራቅ ለሚገኙ የአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች ለእፅዋት ልምላሜና

ለመጠጥ ውሃ አቅርቦት መሻሻል አስተዋፅኦ ይኖረዋል፡፡

በተለይም የክረምቱ ዝናብ በመደበኛ ሁኔታ አስቀድሞ በሚወጣባቸው የሰሜንና የሰሜን ምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች የሚገኘውን እርጥበት በማሳ ውስጥም ሆነ ከማሳ ውጪ ማከማቸትና ሰብሎች ለሚፈልጉት ተጨማሪ ውሃ አቅርቦት እንዲውል ከወዲሁ ማመቻቸት ያስፈልጋል፡፡ በሌላ በኩል ከክረምት ዝናብ መጠናከር ጋር ከባድ ዝናብ በሚጠበቅባቸዉ ስፍራዎች ላይና በተከታታይ እርጥበት እያገኙ ባሉ አካባቢዎች እርጥበቱ ከመጠን በላይ የሚሆን ሲሆንና፤በዚህም ምክንያት ውሃ ማሳ ላይ እንዳይተኛ ቦይ በማውጣት፣ የማንጣፈፍና የመከላከል ስራ በመስራት እንዲሁም በአንዳንድ አካባቢዎች ከእርጥበት መብዛት ጋር የአረም መከሰትና አልፎ አልፎ በየጣልቃው ከሚኖረው ሙቀት ጋር የፀረ ሰብል ተባይ መፈጠር ሊኖር ስለሚችል ከግብርና ባለሙያ በሚያገኙት ምክረ ሀሳብ በመደገፍ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በተጨማሪም የሚጠበቀው ከባድ ዝናብ በረባዳማ፣ ውሃ ገብና በወንዝ ዳርቻ ባሉ ማሳዎች ላይ በሰብሎች፣ በእንስሳትና በንብረት ላይ ጉዳት ሊያስከትል ስለሚችል በተጠቀሱት አከባቢዎች ተገቢው የመከላከል እርምጃ ቢወሰድ ሊደርስ የሚችለውን ጉዳት መቀነስ ያስችላል።

## እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 31/2023 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በውሀው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በመደበኛ ሁኔታ የኦገስት ወር የተሻለ እርጥበት ሁኔታ ሁሉንም የክረምት እርጥበት ተጠቃሚ የሆኑ ተፋሰሶች በመጠንም ሆነ በሥርጭት ከፍተኛ መጠን የሚደርሱበት ወር ነው፡፡ በመጪው በኦገስት ወር በአብዛኛው የክረምት እርጥበት ተጠቃሚ በሆኑት የሀገሪቱ ተፋሰሶች ላይ በምዕራብ፣ በሰሜን ምዕራብ፤ በደቡብ ምዕራብ ፤ በመካከለኛው እንዲሁም በሰሜን ምስራቅ የሀገሪቱ ተፋሰሶች ላይ የእርጥበት ሁኔታው እየተጠናከረ እንደሚሄድ ይጠበቃል፡፡ በዚህም መሰረት በአብዛኛው አባይ፣ ተከዜ፣ አዋሽ፣ ባሮአኮቦ፣ ኦሞጊቤ፣ አዋሽ፣ አፋር ደናክል፣ የላይኛው እና የመካከለኛው፣ የስምጥ ሸለቆ፣ የላይኛው ዋቢ ሸበሌ ና የገናሌ ዳዋ ተፋሰሶች ላይ የተሻለ የእርጥበት ሁኔታ እንደሚያገኙ የሚጠበቅ ሲሆን፤ ይህም ሁኔታ ለውሃ ሀብት መጨመር አዎንታዊ ጎን ይኖረዋል፡፡ በሌላ በኩል ሊኖር ከሚችለው ከፍተኛ እርጥበት ጋር ተያይዞ ለጎርፍ ተጋላጭ በሆኑ ተፋሰሶች እና ንዑስ ተፋሰስ ላይ ቅጽበታዊ ጎርፍ፣ የመሬት መንሸራተት እና የወንዞች ሙላት ሊከሰት ስለሚችል የሚመለከታቸው አካላት እንዲሁም ማህበረሰቡ በሰውም ሆነ በንብረት ላይ ሊደርስ የሚችለው ጉዳት ለመቀነስ አስፈለጊውን ቅድመ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡